# ይህም ተብሎ ነበር

## ለጉዶቹ

ከ ሀማ ቱማ   በ1986 ዓ. ም.

በክህደት ላይ ውሸት፣

በቅጥፈት ላይ ክህደት፣

እየጨማመሩ፤

ዛሬም እንደትላንት፣

ጭምልቅ ጭምልቅ ያሉ፤

ታሪክ ብለው ውሸት፣ ለሚቀላምዱ፣

ያልነበሩበትን፣ ፈጠርነው የሚሉ፣

እኒያ የጉድ ጉዶች፣

ሁሉም ከሀዲዎች።

ጥይት ሳይተኩሱ፣ ጦር መሪ የሆኑ፣

በተመለመሉ፣ መስራቾች ነን ያሉ፣

ክህደት ለምዶባቸው፣ ጌታ የቀየሩ፤

ስንቱን አስፈጅተው፣

ከአጥፊም ተዋልደው፣

ሌላን የሚከሱ፣

ለገንዘብ ለሹመት፣

ትላንት የተፉትን፣ ውግዘት የሰጡትን፣

መልሰው የሚያቅፉ፤ መልሰው ሚልሱ፣

ከእግሩ የሚደፉ።

እኒያ የጉድ ጉዶች!

በክህደት ላይ ውሸት፤ በቅጥፈት ላይ ክህደት፣

እየጨማመሩ፣

ሀገር የሚያጠፉ፣

ወገን የሚገድሉ፣

ለጸረ ሕዝብ መንጋ፣ መሳሪያ የሚሆኑ፣

ሁሉም ከሀዲዎች!

መጋኛ ወያኔ፣

የታሪክ ትቢያዎች።